# የኢትዮጵያ ስፖርት ጋዜጠኞች ማኅበር
# መተዳደሪያ ደንብ

መመሪያ

1. ማህበሩ የሚከተሉት የአመራር አካላት ይኖሩታል

    ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ

    ለ. ኦዲተር

    ሐ. ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና

    መ. ሌሎች ሰራተኞች ይኖሩታል

## <u>አንቀፅ 1: መቋቋም</u>

የ<u>ኢትዮጵያ ስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር</u> የተባለ ማህበር

በ<u>ነሐሴ 14 ቀን 2004</u> ዓ.ም ተቋቁሟል::

## <u>አንቀጽ 2: ስያሜ</u>

1. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመው ማኅበር የ<u>ኢትዮጵያ ስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር</u> በሚል የሚጠራ ሲሆን ከዚህ በኋላ «ማኅበር» ተብሎ ይጠቀሳል::

## <u>አንቀጽ 3: ዓላማ</u>

የማኅበሩ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

- ሀ. በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ የስፖርት ጋዜጠኞችን ሙያዊ መብት ከጥሰት መከላከል
- ለ. የሃገሪቱ የስፖርት ጋዜጠኞች ለሃገሪቱ ስፖርት እድገት የበኩላቸውን ገንቢ ሙያዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማገዝ
- ሐ. በአቅም ግንባታ ስራዎች የሃገሪቱ የስፖርት ጋዜጠኞች ሙያዊ ብቃት እንዲያድግ መጣር

## <u>አንቀጽ 4: የበጀት ዓመት</u>

የማኅበሩ የበጀት ዓመት እንደ ኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ከሐምሌ 1 - ሰኔ 30 ይሆናል::

## <u>አንቀጽ 5: ትርጉም</u>

1. «ማኅበር» ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የተቋቋመው የ<u>ኢትዮጵያ ስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር</u> ነው::
2. «ጠቅላላ ጉባኤ» ማለት መስራች አባላትን፣ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች አባላትን ያቀፈ የማኅበሩ የበላይ አካል ነው::

## <u>አንቀጽ 6: መደበኛ አባላት</u>

1. መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በጠቅላላው ጉባኤ ውሳኔ ተቀባይነት ያገኙ አባላትን ይይዛል::

2. የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ/ የምታሟላ ማንኛውም/ዋም ኢትዮጵያዊ/ት ሰው መደበኛ አባል መሆን ይችላል/ ትችላለች::

ሀ. በማኅበሩ አላማና ግብ የሚያምን/ የምታምን፤

ለ. ዕድሜው/ዋ ከ15 ዓመት በላይ የሆነ/ች፤

ሐ. የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው የሚወጡ የሥነ-ምግባር ደንቦችን የሚቀበል/የምትቀበልና ተግባራዊ የሚያደርግ/ የምታደርግ፣

መ. በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ በየጊዜው ስምምነት የሚደረግባቸውን ክፍያዎችና መዋጮዎች መክፈል የሚችል/ የምትችል

ሠ. በህግ መብቱ/ቷ ያልተገፈፈ፣

3. በህትመት መገናኛ ብዙሃን፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በመረጃ መረብ ላይ የሚሰሩ የስፖርት ጋዜጠኞች፣ አምደኞች፣ ፍሪላንሰሮች፣ የጨዋታ ኮሜንታተሮች፣ የስፖርት ፎቶግራፈሮች፣ የስፖርት ቪዲዮግራፈሮች፣ የስፖርት ብሎገሮች በአባልነት ይያዛሉ::

4. በስፖርት ክለቦች፣ ፌደሬሽኖችና ማህበራት ውስጥ በህዝብ ግንኙነት ክፍል ኃላፊነት ወይም አባልነት በሙሉ ሰዓትም ይሁን በትርፍ ሰዓት የሚሰሩ ባለሙያዎች በስልጠና ጋዜጠኞች ቢሆን እንኳን የማህበሩ አባል ሊሆኑ አይችሉም::

5. በዚሁ አንቀጽ ቁጥር አንድ ላይ የተዘረዘሩትን ስራዎችን የማይሰሩ በጋዜጣና መጽሔት አሳታሚነት፣ በአሳታሚ ድርጅት የአክሲዮን ባለድርሻነት፣ በድረገጽ አሳታሚነት፣ በሬዲዮ ወይም ቴሌቪዥን ጣቢያ ባለቤትነት የሚሰሩ አሰሪዎች የማህበሩ አባላት አይሆኑም::

## አንቀጽ 7: የክብር አባላት

1. የማኅበሩ አባል ያልሆኑና የማኅበሩን ዓላማ ለማስፈጸም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ፤ ማኅበሩ በሚሰራባቸው ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማና የለውጥ አርአያ በመሆን በማኅበሩ አባላት ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የክብር አባል ይሆናሉ::
2. የክብር አባላት በማኅበሩ ውስጥ የመምረጥ የመመረጥና ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም::
3. የክብር አባላት በራስ ተነሳሽነት ካልሆነ በቀር የአባልነት መዋጮዎችንና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ግዴታ አይኖርባቸውም::

## አንቀጽ 8: የአባላት መብት

1. ሁሉም መደበኛ አባላት እኩል መብት አላቸው፣

2. የማኅበር አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ሰው የማይተላለፍ
የግል መብት ነው::
3. ማንኛውም የማኅበሩ መደበኛ አባል:-
ሀ. ለማኅበሩ ዓላማና ተልዕኮዎች መሳካት የሚጠቅሙ
ማናቸውንም አይነት ስራዎች የመስራት፣
ለ. የመምረጥ፣ የመመረጥና ስለማኅበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውም
መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣
ሐ. በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ የመገኘት፣ ስለማህበሩ እንቅስቃሴ
አስተያየትና ድምፅ የመስጠት መብት አለው/አላት::
መ. ማንኛውም የማኅበሩ መደበኛ አባል አባልነቱ እንዲቋረጥ
የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት በስራ አስፈፃሚ
ቦርድ የመስማማት መብት አለው::

## አንቀጽ 9: የአባላት ግዴታ

1. ማንኛውም አባል የአባልነት መዋጮውን ወር በገባ በመጀመሪያው እስከ ስምንተኛው ቀን ድረስ መክፈል አለበት/አለባት
2. አንድ አባል ከአባልነት ከመሰናበቱ/ቷ በፊት የሚፈለግበትን/የሚፈለግባትን
ዕዳ መክፈል ይኖርበታል/ይኖርባታል::
3. ማንኛውም አባል የማኅበሩን የመተዳደሪያ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባኤ
የሚወጡ መመሪያዎችና ውሳኔዎችን ማክበር አለበት/ አለባት፣
4. ማንኛውም አባል የማህበሩን ዓላማና የገባቸውን፣ የገባችውን ግዴታዎች
ማክበር፣ የማኅበሩን ንብረት የመንከባከብና የሚጠበቅበትን
አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት/ አለባት፣
5. በማኅበሩ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ
አለበት/አለባት::

## አንቀጽ 10: የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች

የአባልነት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች

1. የማህበሩ ወርሃዊ መዋጮ ብር 25 (ሃያ አምስት ብር) ነው::
2. ማንኛውም አባል ወርሃዊ መዋጮውን በኢትዮጵያ አቆጣጠር ወር በገባ እስከ ሰባተኛው ቀን ድረስ ያለ መቀጮ ይከፍላል::
3. ሳይከፍል ጊዜውን ያሳለፈ አባል ከመደበኛው ክፍያ በተጨማሪ በየወሩ ብር 10 (አስር ብር) ቅጣት ይጣልበታል::

## አንቀጽ 11፡ አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

አንድ የማኅበሩ አባል አባልነቱ/ቷ የሚቋረጠው፣

1. ሲሞት/ ስትሞት፣
2. መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለፀው መሠረት ወይም በሌላ አጥጋቢ
   ምክንያት ከአባልነት እንዲሰናበት/ እንድትሰናበት ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን፣
3. የማኅበሩን ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ
   መሳተፉ/ፏ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣

4. ለማህበሩ ዓላማ መሳካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሳትፎ ለማድረግ ፍቃደኛ ሳይሆን/ሳትሆን ሲቀር/ስትቀር እና ይኸውም በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሲወሰን
5. መዋጮውን ለስድስት ወራት ያህል ባለመክፈሉ/ሏ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከአባልነቱ/ቷ ሲሰናበት/ስትሰናበት
6. አንድ አባል መዋጮ የመክፈሉን ግዴታ ሳይወጣ አልያም በተለያዩ ምክንያቶች ከማህበሩ ከተሰናበተ በኋላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተጸጽቶ በይፋዊ ደብዳቤ ይቅርታ ሲጠይቅና በጠቅላላ ጉባዔው ተቀባይነት ካገኘ ውዝፉን የአባልነት መዋጮ እንዲከፍልና ከዚያም ለስድስት ወራት ከማህበሩ የሚያገኘውን ጥቅም እንዲያጣ ተደርጎ ወደ አባልነት ይመለሳል፡፡
7. በፈቃደኝነት አሊያም በአስገዳጅ ሁኔታ ከማህበሩ የወጣ ወደ ማህበሩ አባልነት መመለስ ቢፈልግ እንደ አዲስ አባል ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል በድጋሚ አባል መሆን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 12 የማኅበሩ አደረጃጀት

1. ማኅበሩ የሚከተሉት የአመራር አካላት ይኖሩታል
   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ
   ለ. ኦዲተር
   ሐ. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና
   መ. ሌሎች ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡
2. ማኅበሩ በሚከተለው መልኩ የተዋቀረ ነው፡-




3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆነ ማናቸውም ሰው በተጨማሪ ኦዲተር ሆኖ ሊሰራ አይችልም፡፡

## <u>አንቀጽ 13፡ የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር</u>

1. ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 5 ላይ የተጠቀሱትን መደበኛ አባላት የሚያካትት ሆኖ በህግና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   - ሀ. ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩ የበላይ አካል ነው፣
   - ለ. የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣
   - ሐ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የማህበሩን ኦዲተር ይመረጣል፣
   - መ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን፣ የጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይሾማል፣ ይሽራል፣
   - ሠ. የማኅበሩን ዋና መስሪያ ቤት የመለወጥና ቅርንጫፎች የመክፈት የመጨረሻ ውሳኔ ያሳልፋል፣
   - ረ. ማኅበሩን ማፍረስና ንብረት ማጣራት ላይ ይወስናል፣
   - ሰ. የማኅበሩን ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርትና ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል፣
   - ሸ. ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምን በመመርመር እቅድና በጀት ያፀድቃል፣
   - ቀ. በማኅበሩ የፖሊሲና የስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣
   - በ. የማኅበሩ አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
   - ተ. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 9 በተገለፀው መሠረት ግዴታውን

ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይወስናል፣

ቸ. የአባላት መዋጮ ሌሎች ክፍያዎችንና የቅጣት መጠን ላይ ይወስናል፣

ኀ. የማኀበሩ ሂሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣

ነ. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣

ኘ. ማኀበሩ ከሌሎች ማህበራት ጋር ህብረት ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም የመለወጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

አ. በማኀበሩ ለሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ማኀበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል::

2. ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሠ)፣ (በ)፣ (ቸ) እና (ኀ) መሠረት የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለማኀበሩ አካላት ወይም ለሚያቋቁመው ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ በውክልና ማስተላለፍ ይችላል::

3. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል::

<u>አንቀጽ 14: የጠቅላላ ጉባዔ ድምጽ አሰጣጥ</u>

1. ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ/ታ ድምፅ በሚሰጥበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው፣ የምትሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል::
2. ማንኛውም የማኀበር አባላት እኩል ድምጽ አላቸው::
3. ጠቅላላ ጉባኤው በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም አካል በስብሰባ ላይ ራሱ/ሷ ተገኝቶ/ታ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል/ባታል::
4. የድምጽ አሰጣጡ ሥነ-ሰርዓት ፍትሀዊ ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል::
5. ከጠቅላላው ጉባኤ የተለየ ሃሳብ ያለው/ያላት የማህበር አባል የልዩነት ሃሳቡን/ቧን በቃለ ጉባኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል/ ትችላለች::
6. ማንኛውም መደበኛ የማህበር አባል በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሳኔ የሃገሪቱን ህግጋት ወይም የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ይጥሳል ብሎ/ላ ሲያምን/ስታምን ለኤጀንሲው ሊያመለክት/ልታመለከት ይችላል/ ትችላለች::

<u>አንቀጽ 15: የጠቅላላ ጉባዔው አመራር አካላት ስልጣንና ተግባራት</u>

ጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የሚኖረው ሲሆን ስልጣንና ተግባራቸውም የሚከተለው ነው፣

ሀ. የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባዎች ይጠራል/ትጠራለች ከፀሃፊው/ዋ ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጀል/ታዘጋጃለች፣

ለ. የጉባኤውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል/ትመራለች፣

ሐ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚያወጣቸውን ደንቦችና የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል/ትከታተላለች፣

መ. ጉባኤው ያፀደቃቸው ዓመታዊ የስራ ክንውን፣ የስራና የኦዲት ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት እና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችና ለለጋሾች እንዲደርሱ ያደርጋል/ታደርጋለች፣

ሠ. ለጉባኤው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለፀሐፊው በአጀንዳነት ያስይዛል፣

2. ምክትል ሰብሳቢ

ሀ. ሰብሳቢው/ዋ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ ተክቶ/ታ ይሰራል/ ትሰራለች፣

ለ. በስብሳቢው/ዋ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ስራዎች ያከናውናል/ታከናውናለች፣

3. ፀሐፊ

ሀ. ከሰብሳቢው/ዋ ጋር በመሆን ለጉባኤው አጀንዳዎች ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች፣

ለ. የጉባኤውን ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል/ትይዛለች፣

## አንቀጽ 16፣ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ

1. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ሊቀመንበር ጠሪነት የሚካሄድ ሆኖ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ መካሄድ ይኖርበታል::
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ሊቀመንበር በ30 ቀናት ውስጥ ስብሰባ ያልጠራ እንደሆነ ኤጀንሲው በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ አባላት ጠያቂነት በሊቀመንበሩ አማካኝነት ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ሊጠራ ይችላል::

3. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከሆነ ኤጀንሲው የጠቅላላ ጉባኤ ሊቀመንበር የሚሆን/ የምትሆን ሰው ለምርጫ ሊያቀርብ ይችላል::
4. የማኅበሩ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በፕሬዚዳንቱ ወይም ሊቀመንበሩ ከማኅበሩ 10 ከመቶ የሚሆኑት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊካሄድ ይችላል፤
5. ለጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ አስራ አምስት የስራ ቀናት ለአስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከአምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ በፊት አባላት የስብሰባው ዝርዝር ጉዳይ፣ ቦታውን፣ ቀኑን፣ ጊዜውን እንዲያውቁት ይደረጋል::
6. የማኅበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል::
7. ከላይ በአንቀጽ 6 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ምልዓተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ካልተሟላ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚቀጥለው ስብሰባ በተገኙት አባላት እንዲካሄድ ያደርጋል/ታደርጋለች::
8. በጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው በአጀንዳነት ተይዘው ለውይይት ይቀርባሉ፣ ማንኛውም ጉዳይ በአጀንዳ እንዲያዝለት የሚፈልግ አባል ጠቅላላ ጉባኤ ከመሰብሰቡ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ለጉባኤው ፀሐፊ/ፕሬዚዳንቱ/ የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ በፅሁፍ ይህንኑ ማስታወቅ ይኖርበታል/ይኖርባታል::

## አንቀጽ 17: የምርጫና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት

1. ማኅበሩ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ይሆናል፣
2. ጉባኤው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲሄድ ያደርጋሉ፣
3. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወሰኑ አድርጐ ምርጫውን ያስፈጽማል፣
4. ጠቅላላ ጉባኤው የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተሻሩ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተጓዳሉ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን ለመተካት እንደ አስፈላጊነቱ የአስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፣
5. የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ተመራጮች በድጋሚ እንዲያገለግሉ ከተፈለገ በጥቆማ ለውድድር ቀርበው በድምጽ ብልጫ መመረጥ ይኖርባቸዋል፣ ሆኖም ለ3ኛ ጊዜ ለመመረጥ አንድ የምርጫ ዘመን /4 ዓመት/ መቆየት ይኖርባቸዋል::

6. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምፅ እኩል ሲሆን ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፣
7. የማኅበሩ የስብሰባ ሥነ-ስርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆዎችን የተከተለ መሆን አለበት፣
8. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለኮሚቴ ምርጫ በዕጩነት ማቅረብ አይችሉም፣ ሆኖም ግን የጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት በዕጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፣
9. አስመራጭ ኮሚቴው አዲሶቹ ተመራጮች 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስራቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣
10. የቀድሞ ተመራጮች በምርጫ ከተሰናበቱበት ዕለት ጀምሮ ከጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ውጪ ከርክክብ በስተቀር ስራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፣
11. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳነት ቀርበው ያፀደቁና ያልፈሰሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሳኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

<u>አንቀጽ 18፡ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት</u>

1. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤው የሚቋቋምና ተጠሪነቱም ለዚሁ አካል ሆኖ የማኅበሩን የዕለት ተዕለት ስራ ያከናወናል።
2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።
    ሀ. የማኅበሩን ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት በጀት ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል፣
    ለ. የማኅበሩን ዓመታዊ የስራ መርሀ ግብርና የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅድ አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል፣
    ሐ. የማኅበሩን ዓላማዎች ለማስፈፀም የገቢ ምንጮችን የገንዘብ፣ የጉልበት ወይም የማቴሪያል ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ያፈላልጋል፣
    መ. የማኅበሩን ፖሊሲ በማመንጨት ያቀርባል፣
    ሠ. ሰራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፣ ዝውውር፣ እድገት፣ ስንብት፣ ደመወዝና አበል ይወስናል፣
    ረ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎች በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
    ሰ. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች እንዲከፈቱ ለጠቅላላ ጉባኤው አቅርቦ ያስወስናል፣

ሸ. የአባልነት ግዴታቸውን ያልተወጡ አባላት እንዲሰረዙ ለጠቅላላ ጉባኤው የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣

ቀ. የራሱን የአሰራር ስነ ስርዓት ያወጣል፣

በ. በጠቅላላ ጉባኤው የተሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፣

ተ. የማኅበሩን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣

## አንቀጽ 19፡ የስራ አስፈፃሜ ኮሚቴ አባላት

1. የስራ አመራር ቦርድ ከ5-7 አባላት ይኖሩታል፣ (ቢሆንም የቦርዱ ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲያመች ጐዶሎ መሆን ይኖርበታል)
2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. ፕሬዚዳንት

ለ. ምክትል ፕሬዚዳንት

ሐ. ፀሐፊ

መ. ሂሣብ ሹም

ሠ. ገንዘብ ያዥ፣ እና

ረ. ሌሎች ሁለት አባላት ይኖሩታል፡፡

3. ፕሬዝዳንቱ/ቷ

በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን የሚከተሉትን ስራዎች ያከናውናል፡፡

ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ የሚያቋቁማቸውን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎችን በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡

ለ. ማህበሩን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፡፡

ሐ. በማኅበሩ ስም የተከተፈውን የባንክ ሂሳብ ቼኮችንና የወጪ ሰነዶችን ከሂሳብ ሹሙ ጋር በመሆን በጣምራ ይፈርማል፡፡

መ. ለማኅበሩ ስራ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ይፈቅዳል፡፡

ሠ. የ3 ወር፣ የ6 ወርና ዓመታዊ የስራ፣ የፋይናንስ ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለስራ አስፈፃሚ ኮሜቴው ያቀርባል፡፡

ረ. በማኅበሩ ስም ደብዳቤዎችን ይፈርማል፡፡

ሰ. ሂሳብ ሹምና ገንዘብ ያዡን ጨምሮ በስሩ የሚገኙቱን ሰራተኞች እያስተባበረ እየተከታተለና እየተቆጣጠረ የማህበሩን የዕለት ተዕለት ስራ እንቅስቃሴ ይመራል፡፡

ሸ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን በማስፈቀድ በማህበሩ ስም ንብረት ለመግዛትና ለመሸጥ የሚያስችሉ ውሎችን ይቀጥላል፡፡

ተ. በጠቅላላው ጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በተግባር ላይ ያውላሉ፡፡

በ. ሌሎች ለስራ አስፈፃሚው የሚሰጠውን ስራ ያከናውናል::

4. ምክትል ፕሬዚዳንቱ/ቷ፣

ሀ. ፕሬዚዳንቱ/ቷ በማይኖሩበት ጊዜ ፕሬዚዳንቱን/ቷን ተክቶ/ታ ይሰራል/ትሰራለች::

ለ. በፕሬዝዳንቱ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡ ተጨማሪ ስራዎችን ያከናውናል::

5. ፀሐፊው/ዋ

ሀ. የስራ አስፈፃሚ ኮሜቴ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል::

ለ. ከስራ አስፈፃሜ ኮሚቴው በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የማኅበሩን የመፃፃፍ ግንኙነት ስራዎች ያከናውናል::

ሐ. የስራ አስፈፃሚውን አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ቃለጉባኤ ይይዛል::

መ. የማህበሩን ማህተም፣ ሰነድና መዛግብት ይይዛል::

ሠ. የአባልነት ማመልከቻዎችን ይቀበላል::

6. ሒሳብ ሹም

ሀ. የማኅበሩን ገቢና ወጪ ሂሳብ በበላይነት ይቆጣጠራል::

ለ. የማኅበሩ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰው በታወቀ የሂሳብ አሰራር ደንብ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል::

ሐ. በማኅበሩ ስም የተከፈተውን የባንክ ሂሳብ ቼክና የወጪ ሰነዶች ላይ ከፕሬዚዳንቱ ጋር ወይም ከምክትል ፕሬዚዳንቱ ጋር በጣምራ ይፈርማል::

መ. የማህበሩ የሂሳብ መዛግብት በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል::

ሠ. የሂሳብ መዝገብ፣ ገቢና ወጭ፣ ሀብትና ዕዳን ያካተተ ሰነድ ያዘጋጃል::

ረ. ማኅበሩ ገቢ በሚያስገኙ ስራዎች ላይ በሚሰማራበት ጊዜ ለዚሁ ስራ የሚውሉ የተለያዩ የሂሳብ መዛግብት እንዲያዙ ያደርጋል::

6. የማኅበሩ ገንዘብ ያዥ፣

ሀ.የማኅበሩን ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል::

ለ. የተሰበሰበውን ገንዘብ አገር ውስጥ በሚገኝ ባንክ ገቢ ያደርጋል ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣

ሐ. ለስራ ማስኬጃና ለማህበሩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚሆን ከብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ያልበለጠ ገንዘብ ይይዛል::

መ. ከሂሳብ ሹሙ ጋር የወጪና የገቢ ሂሳብ በየወሩ ያመሳክራል::

ሠ. የማኅበሩን ቼክ ይይዛል::

ረ. በጣምራ ፊርማ በሂሳብ ሹሙና በፕሬዚዳንቱ በወጪ ሰነድ

ሲታዘዝ ወጪ ያደርጋል::

## <u>አንቀጽ 20: የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ፣ የድምፅ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓትና የአባላት የአገልግሎት ዘመን</u>

1. የኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በዓመት አራት ጊዜ የሚከናወን ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲኖር ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. አስቸኳይ ስብሰባ በፕሬዚዳንቱ ወይም ምክትል ፕሬዚዳንቱ ሊጠራ ይችላል፣
3. ከአባላቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ ድጋሚ ለስብሰባ ጥሪ ይደረጋል:: በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፣
4. ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ይተላለፋሉ፤ ድምፅ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ፕሬዚዳንቱ የደገፈው ሃሳብ ይፀናል፣
5. የኮሚቴ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለአራት ዓመት ይሆናል:: ሆኖም አንድ የኮሚቴ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፣
6. የኮሚቴ አባላት ያለደመወዝ ያገለግላሉ፣ ሆኖም ለማኅበሩ ስራ ለሚያወጡት ወጪዎች ማካካሻ ይከፈላል::

## <u>አንቀጽ 21: የኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር</u>

1. የማኅበሩ ኦዲተር የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ወይም የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሊሆን አይችልም::
2. ኦዲተሩ ቀጣሪነቱ ለጠቅላላው ጉባኤ ሆኖ፤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል::
3. የማኅበሩን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፣
4. የማኅበሩ የስራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣
5. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሠረት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል፣

## አንቀጽ 22: የማኅበሩ የገቢ ምንጭ

የማኅበሩ ዋና የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ከህዝባዊ መዋጮ፣ ከገቢ ማስገኛ ስራዎችና ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 23: የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል

1. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሃሳብ ጠቅላላ ጉባኤው አባላት 1/4ኛ ባላነሱ አባላት ጠያቂነት በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል፡፡
2. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሃሳብ በጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ሆኖ የማሻሻያ ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ ወይም ፕሬዚዳንት የጉባኤው ጥሪ ከመሰራጨቱ በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. የመተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻለው የማሻሻያ ሃሳቡ ከግማሽ በላይ አባላት በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ 3/4ኛ ድምፅ ሲያገኝ ነው፡፡
4. የመተዳደሪያ ደንቡ እንዲሻሻል የተላለፈውን ውሳኔ ኤጀንሲው ያላፀደቀው እንደሆነ ባልፀደቀበት ምክንያት ላይ የሚወያይ ስብሰባ ይቀጠራል፡፡
5. እንዲሻሻል የተወሰነው የመተዳደሪያ ደንብ በኤጀንሲው በኩል ታይቶ ከመፅደቁ በፊት ስራ ላይ ሊውል አይችልም፡፡

## አንቀጽ 24: ስለማኅበሩ መዋሃድና መለወጥ

1. ማህበሩ ወደ ተለያዩ ማህበራት የሚከፋፈለው፣ ከሌላ ማህበር ጋር የሚዋሃደው ወይም ወደ በጐ አድራጎት ድርጅትነት የሚለወጠው በጠቅላላ ጉባኤው በ3/4ኛ ድምፅ ሲወሰን ነው፡፡
2. ከማህበሩ ጋር የሚዋሃደው ማኅበር ጋር የሚደረገውን ድርድር የሚያከናውነው ኮሚቴ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ፀሀፊና የማህበሩን ፕሬዚዳንት ማካተት ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 25: ስለማኅበሩ መፍረስ

1. ማኅበሩ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማኅበሩ እንዲፈርስ በ3/4ኛው ድምፅ ሲወስኑ ነው፡፡
2. ጠቅላላ ጉባኤው ማኅበሩን ለማፍረስ ከወሰነበት ቀን አንስቶ ስድስት ወራት ሳያልፍ የማህበሩ ፕሬዚዳንት የንብረት ቆጠራ /inventory/ ሰርቶ ከማፍረስ ውሳኔው ጋር በማያያዝ ለበጐ አድራጐት ድርጅትና ማህበራት ኤጀንሲ ያቀርባል፡፡

3. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ በወሰደው ውሳኔ ላይ የማህበሩን ንብረት ሊረከብ ይገባዋል የሚለውን የበጐ አድራጐት ድርጅት ወይም ማኅበር ወይም የመንግሥት አካል ሊያመለክት ይችላል፡፡

<u>አንቀጽ 26፡ የመተዳደሪያ ደንብ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ የመተዳደርያ ደንብ በበጐ አድራጉት ድርጅቶችና ማኅበራት ኤጀንሲ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር
ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ - አዲስ አበባ